**ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት**
**ፒተር ኒውሻም**
የፖሊስ ቺፍ

**የኮሚኒኬሽንስ ቢሮ**
**ደስቲን ስተርንበክ**
ዳይሬክተር

# ዜናዎች

ባፋጣኝ ይለቀቅ

*የህዝብ መረጃ ቢሮ፡* 202- 727-4383

ማርች 18፣ 2020

## ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት በኮቪድ-19 ጊዜ የሚያደርጋቸው የአሰራር ማስተካከያዎች

(ዋሺንግተን ዲሲ)- ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት (ኤም.ፒ.ዲ.) ቀውሶች በሚኖሩባቸው ሁኔታዎች ደረጃቸው የጠበቁ ሞያዊ ምላሾች በመስጠት ረገድ ኩራት ይሰማዋል፣ ባሁኑ ጊዜ ባለው የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜም ደረጃቸው የጠበቁ ሞያዊ ምላሾች መስጠቱን እንቀጥላለን። ይህ በየጊዜው የሚለዋወጥ ሁኔታ ሲሆን ኤም.ፒ.ዲ. ለማህበረሰባችን የምንሰጠው ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት ሳይቋረጥ ተጋላጭነትን ለመገደብ የበኩላችን እንድንሰራ እንጠየቃለን። በተጠራንበት ጊዜ አስቸኳይ አገልግሎቶች ማቅረቡ እንቀጥልበት ዘንድ ኤም.ፒ.ዲ. ጤናማ ሰራተኞች እንዲኖሩት ያስፈልጋል። ለማህበረሰቡና ለአባሎቻችን ለጊዜው መስተካከል የሚችሉ የተወሰኑ የክወና እርምጃዎች ለይተናል።

የኤም.ፒ.ዲ. ተቋማት ክፍት መሆናቸው እንደሚቀጥሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፣ ነገር ግን ሊመጣ ከሚችል ተጋላጭነትና የኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ስርጭት ለመከላከል፣ የአሰራር ማስተካከያዎች ተግባራዊ ሆነዋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ መስፋፋቱን ይቀጥላል። በተጨማሪ፣ **የፖሊስ አገልግሎት ይሰጥዎት ዘንድ ከደወሉና የጉንፋን-አይነት (ፍሉ-ላይክ) ወይም እንደነ ትኩሳት፣ ሳልና የትንፋሽ እጥረት የመሳሰሉ የኮቪድ-19 ምልክቶች እየታየብዎት ከሆነ ሲደውሉ፣ የመጀመሪያ መላሾች ሲመጡ ተገቢ የደህንነት ቅድመ-ጥንቃቄ ያደርጉ ዘንድ፣ ለአስተላላፊ (ዲስፓቸር) ይጠቁሙ።**

የሚከተሉት የአሰራር ማስተካከያዎች በኤም.ፒ.ዲ. ተደርገዋል፡

**ለአገልግሎት ሲደውሉ**

- አገልግሎት መስተጋብር ለማግኘት ሲደውሉ፣ ኦፊሰሮቹ የሚቻል ሲሆን **ከተበዳይ ነኝ ባይ ከቤት ውጪ ሆነው ለመነጋገር** ይጠይቃሉ። የህዝብ ጤና ባለ ስልጣናት ከሚሰጥዋቸው ምክሮች ጋር የተጣጣመ ርቀት ላይ ሆነን ለማነጋገር እንሞክራለን፣ የህዝብ ትብብር ይኖረን ዘንድም እንጠይቃለን።

- የዲ.ሲ. ፍርድ ቤት የፍርድ ቤቱን ስራዎች ከገደበበት ትእዛዝ ተከትሎ፣ ኤም.ፒ.ዲ. ዲስትሪክት ጣቢያዎች ታሳሪዎች በሚቀጥለው ቀን ፍርድ ቤት እስኪደርሱ ድረስ እስር ውስጥ ከሚቆዩ እስከ **የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀን ድረስ በሳይቴሽን መፈታት** የሚችሉበት መወሰኛ መስፈርት አስፍቷል።

# ዜናዎች

ባፋጣኝ ይለቀቅ

*የህዝብ መረጃ ቢሮ፡* 202- 727-4383

- በዲፓርትመንት ኦፍ ሞቶር ቨሂክልስ አንዳንድ አገልግሎቶች ለጊዜ በመታገታቸው ምክኒያት ኦፊሰሮች **የጥሰቶች ማስጠንቀቂያ ማስታወቂያ የሚሰጡት** በማርች 1፣ 2020 ወይም በኋላየአገልግሎት ጊዜያቸው የሚያበቃ የዲ.ሲ. የመኪና ምዝገባና መንጃ ፈቃዶች/ፐርሚትስ ብቻ ነው።

- ዜጎች ለ**ኦፊሰሮችና ለመርማሪዎች በጽሁፍ በኢሜይል መግለጫቸው እንዲልኩ** እናበረታታለን። ኦፊሰሮች ለዜጎች ትክክለኛ ኢሜይል አድራሻ እንዲቀርብላቸው ያደርጋሉ፣ ለሁሉም የሚደርሷቸው ኮሚኒኬሽኖች እንደደረሳቸው የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ይልካሉ።

## የማህበረሰብ መስተጋብሮች

- በኤም.ፒ.ዲ. ተቋማት የሚደረጉ ስብሰባዎችና ዝግጅቶች ለጊዜው ታግደዋል።

- አሁንም ቢሆን ጥያቄዎቻችሁና የሚያሳስቡዋችሁ ነገሮች ለመመለስ ኤም.ፒ.ዲ. ሰራተኞች ዝግጁ ናቸው፣ ከሚመለከታቸው ክፍል ወይም ዲስትሪክት ጣቢያ ጋር ይገናኙ።

- የማህበረሰብ ፒ.ኤስ.ኤ. ስብሰባዎች በኮንፈረንስ ኮል በኩል እንዲደረግ ከተፈለገ በተመደበልዎ የዲስትሪክት ኮሚኒቲ አውትሪች ኮኦርዲኔተር በኩል ዝግጅት ያድርጉ።

## የፖሊስ ሪፖርቶች ፋይል ማድረግና ሪፖርቶቹን ማግኘት

- **የፖሊስ ሪፖርት በኦንላይን ፋይል ማድረጉ ያስቡበት** ኤም.ፒ.ዲ. አስቸኳይ-ላልሆኑ ፍጻሜዎች በኦንላይን ሪፖርት የሚደረግበት መሳሪያ አለው፣ https://mpdc.dc.gov/service/file- police-report-online. በመጎብኘት ማግኘት ይቻለል። አስቺኳይ ነገር ሲያጋጥም ዜጎች 9-1-1 መደወል ይኖርባቸዋል። በተጨማሪ ዜጎች የከተማ አገልግሎቶችና መረጃ በቀን ለ24 ሰአታት እርዳታ ለመጠየቅ 3-1-1- ይደውሉ።

- **በቴሌፎን ሪፖርቲንግ ዩኒት ሂደት የሚደረግባቸው የ9-1-1 እና 3-1-1 የስልክ ጥሪዎች ተዘርግቷል ።** ግራ መጋባትን ለመቀነስ፣ በኦንላይን ሪፖርት የሚያደርጉ ተጠቃሚዎች አስቸኳይ ወይም አስቸኳይ-ያልሆነውን ክስተት በቴሌፎን ሪፖርቲንግ ዩኒት (ቲ.አር.ዩ.) ሪፖርት **ማድረግ የለባቸውም።**
    - o አንድ ክስተት ለቲ.አር.ዩ. ብቁ ለመሆን ክስተቱ የጥቃት ወንጀል፣ በቤተሰብ-ውስጥ የሚደረግ ክስተት ወይም ወንጀል፣ መሳሪያ ያለበት፣ ወይም ከባድ ቁስሎች ያስከተለ መሆን የለበትም። የመጀመሪያ 9-1-1 ሲደወል ተጠርጣሪው ክስተቱ በተደረገበት ቦታ ወይም በአቅራቢያ ካለ የቲ.አር.ዩ. ሪፖርት መጠቀም አይገባም። በመጀመሪያ ጥሪ ቃለ ምልልስ ሲደረግ በማንኛውም ሰአት የፖሊስ ምላሽ የሚያስፈልግበባቸው ሁኔታዎች ካሉ በስልክ-የሚያናግሮት ያለ ሰራተኛ ኦፊሰር ወደ በታው ይልካል።

- o የሚከተሉት ክስተቶች ለቲ.አር.ዩ. ሪፖርትስ ብቁ ናቸው፡
    - የእንስሳት ንክሻዎች
    - የክረዲት ካርድ ማጭበርበር
    - በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት *
    - የህዝብ ወይም የግል ንብረት ማበላሸት
    - የንብረት መውደም *
    - ማጭበርበር
    - ገጭቶ ማምለጥ (ሂት ኤንድ ራን)
    - የማንነት ስርቆት
    - የጉዳት (ኢንጁሪ) ሪፖርት
    - የንብረት መጥፋትና የመለያዎች መጥፋት *
    - የተለያዩ/ተጨማሪ መረጃዎች
    - በሱቅ መስረቅ
    - የታመመ/የተጎዳ ሰው
    - ቀላል ጥቃት
    - የተሰረቁ መኪኖች፣ ብስክሌቶች ወይም መለያዎች
    - ያለ ሙብት ንብረት መውሰድ
    - ስርቆት 1 እና 2 *
    - ከመኪና መስረቅ *
    - የአካላዊ ጉዳት ማስፈራሪያዎች/የቀላል ወንጀል (ሚስደሚነር) ማስፈራሪያዎች

**ማሳሰቢያ- * ምልክት ያላቸው ክስተቶች ለኦንላይን ሪፖርቲንግ ቱል ብቁ መሆናቸው ያሳያል**

- **ሁሉም የፖሊስ ሪፖርቶች ወይም የአደጋ ሪፖርቶች ለማግኘት የሚደረጉ ጥያቄዎች በኢሜይል፣ ስልክ እና ፖስታ በኩል ብቻ** ከኤም.ፒ.ዲ. የህዝብ ሰነዶች ክፍል መደረግ ይኖርባቸዋል። የኤም.ፒ.ዲ. ተቋማት ባሁኑ ጊዜ ክፍት ቢሆኑም ዜጎች አማራጭ መንገዶች እንዲጠቀሙ እንጠይቃለን።
    - o የኢሜይል ጥያቄዎች ለ mpd.public-docs@dc.gov መላክ ይኖርባቸዋል፣ እና ከሚከተሉት መረጃዎች አብዛኛውን ማካተት ይኖርባቸዋል፡
        - ሙሉ ስም
        - ክስተቱ ወይም አደጋው የተፈጸመበት ቀን፣ ሰአትና ቦታ
        - ባለ ስድስት አሀዝ ሪፖርት ቁጥር (ሲ.ሲ.ኤን.)
    - o በስልክ የሚደረጉ ጥያቄዎች ለኤም.ፒ.ዲ. የህዝብ ሰነዶች ክፍል በስልክ ቁጥር 202-727- 4357 መደረግ ይኖርባቸዋል።

**ሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት**
**ፒተር ኒውሻም**
የፖሊስ ቺፍ

**የኮሚኒኬሽንስ ቢሮ**
**ደስቲን ስተርንበክ**
ዳይሬክተር

# ዜናዎች

ባፋጣኝ ይለቀቅ

*የህዝብ መረጃ ቢሮ፡* 202- 727-4383

- በፖስታ የሚላኩ ጥያቄዎች የተመላሽ አድራሻ የተጻፈባቸውና ቴምብር የተለጠፈባቸው ፖስታዎች ያካተቱ መሆን ይኖርባቸዋል፣ ለ ኤም.ፒ.ዲ. የህዝብ ሰነዶች ክፍል በሚከተለው መላክ ይቻላል፡

  Metropolitan Police Department Public Documents Unit
  ATTN: Accident/Incident Reports 300
  Indiana Avenue NW, Room 3075
  Washington, DC 20001

በዚህ ማስታወቂያ ያልተጠቀሰ ማንኛውም አገልግሎት ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ በተለምዶ ይያዝበት በነበረ ሁኔታ ይያዛል።

አሁንም ቢሆን ዲፓርትመንታችን ዋናው ቅድሚያ የምሰጠው ነገር የአባላቶቻችንና የነዋሪዎቻችን ደህንነትና ጤና ነው።
የኮቪድ-19 ስርጭት ለመቆጣጠር ስራችን እየቀጠልን ባለበት ጊዜ ትዕግስትዎን፣ ማስተዋልዎን እና ትብብርዎን እንጠይቃለን።

ለኮቪድ-19 የዲስትሪክት መንግስት እያደረገ ስላለ ምላሽ የቅርብ ጊዜ መረጃ ቢፈልጉ እባክዎ coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።

###